# እስከ መቼ?

ያዝ ለቀቅ ነካ ጣል
ዳር ዳሩን ጥግ ጥጉን ሳልገባ መሃል
ብቅ ጥልቅ፣ በልጭ ድርግም፣ ጭል ጭል
ሲያሰኘኝ አንገት ድፋት
ሲለኝ ደግሞ ደረት ንፋት
አንገት ንቅንቅ
ወገብ ሰበቅ
ከኔ ወዲያ ወደር ለኔ
ጾም ሲባል ከሮብ፣ አርብ እስከ ሰኔ።
አይ ችግር! አይ ምስቅልቀል!
በጨለማና በብርሃን አንድነት ልፈጥር ስከጅል
ጣዖትን ከታቦት ልቀላቅል
አይጣል!

ከመንገዱ ወጥቼ
/አዝማች/ አቅጣጫዬን ስቼ
የታዘዝሁትን ትቼ

ግራ ገብቶኝ ግራ አጋብቼ
መጥገብ ሲገባኝ ከሕይወት ምግብ በልቼ
መርካት ሲገባኝ ከሕይወት መጠጥ ጠጥቼ
መባዘኔ እስከመቼ መራብ መጠማቴስ እስከመቼ
እኮ እስከመቼ?

ገመና ችግር ስሰማ የወንድሜን የእህቴን
ወዲያው ከንፈር ምጥጥ፣ እዝን እዝን
አፍ አውጥቼ ዋ እኔን!
ብዬ ሳስመስል ስደልል
መልካም ደግ ሰው ለመባል
አጋዥነቴን አሳይቼ
ምስጢሩን ሁሉ ሰምቼ
የአንገት በላይ ማጽናናት ሰጥቼ
አገኝ ይመስል ቅድስና ዘወር እልና
ጉድ ገድ መጣበት ጉድ መጣባት ይኸውና
አይ እገሌ አይ እገሊት!

እንደሱ ካለ ከእሷው ዓይነት
አረ በእምዬ ሞት! እንዴት?
ይኸ ይበቃል በእውነት?
እሱ እኮ አይ ሲያማ እሷም እንደርሱ ናት
ወይ ያለባቸው ቅናት!
እያልሁ ቡጭቅ ቡጭቅ
በቢለዋው ምላሴ በስለታምነቱ እውቅ
ትንሽም ሳልሰቀቅ።
ታዲያ እኔ እንዲህ ስናገር
ባልንጀራዬን ሳብጠለጥል ከባድ ቃል ስዘነዝር
ንጹህ ነኝ ብመረመር?
ውስጤ ቢታይ በመሳሪያ
በአጉልቶ ማሳያ
እኮ እኔ ንጹህ ነኝ?
የልብ መርማሪው ቢያየኝ?

አዝ

ዘወትር ቆሜ በአምላክ ፊት
በመቅደሱ በዓውደ ምህረት
ስመላለስ በሥርዓት ስለሌላው ኃጢአት ስተነትን
ሳጠፋ ስሙን ስሟን
ጾም መሻሩን መሿራን
ዘፈን መውደዱን መውደዷን
ሳጋልጥ ስከመነመን
ግን እኔ እጾም ይሆን
አልሰማ ይሆን ዘፈን
በሚያስተምር ጊዜ አምላካችን መድኃኒታችን ክርስቶስ
አይሁድ ባመጡት የዝሙት ክስ
ተዋርደው አፍረው እንደሸሹት
እግሬ አውጭኝ እንዳሉት
እሸሽ ይሆን ርቄ
መልስ ማጣቴን አውቄ
ለሚቀርብልኝ ፍተሻ የማን ይውገራት ጥያቄ

አዝ

ባልንጀራዬን አጣጥዬ እኔ መሻሌን ሰብኬ
እንዲሰማልኝ ዝናዬ እንዲወራልኝ ታሪኬ
ማንም ማንም አይችልም
እገሌም እገሊትም
በዚህ በኩል የሉበትም

አይ እኔ ባገኘው!

ሥልጣኑን ብይዘው

እሠራ ነበር ቀን ከሌሊት

አሳይ ነበር የሰውፐ ዓይነት

አመጣ ነበር ውጤት።

ግና የአበው ቃል ምሳሌው

በተግባር የታየው

ፍተሻውን ያስፈው

ከበሮ በስሙ እጅ ያምር

ሲይዙት ግን ያደናግር

በእኔው ሳይ ሲደርስ እፍር።

ታዲያ እንዲያ በነገር ስኩራራ

ጉድለቴ ሲታይ በጠራራ

ከምን ይሆን የኔ ተራ

ወይ አልሠራ ወይ አሳሠራ

እንዲያው ቆሜ መሃል መንገድ

ሰው እንዳይጓዝ የማግድ

የማደናቅፍ የማናድድ።

ባዶነቴን የማውቅበት

እኔነቴን የማይበት

ዓይነ ልቡና እንዲሰጠኝ

እንጅ ስምኑልኝ

ዳኛ ፊት አታቅርቡኝ

ምናልባት ይሆናልና

የማን ይውገረው ፈተና።

አዝ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ደምስው ይነሱ

ኦስሉ